# ጋዜጣ ነጋሪት ትግራይ

## የትግራይ ነጋሪት ጋዜጣ

ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ

የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

መበል 28ዓመት ቁ.23 መቐለ --/2014ዓ.ም.

ብሓልዮት ቤት ምኽሪ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስቲ ትግራይ ዝወፅአ

28ኛ ዓመት ቁ.23መቐለ --/2014 ዓ.ም.


## ቍፅሪ ኣዋጅ 359/2014 ዓ.ም

## ኣዋጅ ህፁፅ እዋን መንግስቲ ትግራይ ቑፅሪ 358/2013 ዓ.ም ንምንዋሕን ንምምሕያሽን ዝወፀ ኣዋጅ

ህልውናን ድሕንነትን ህዝቢ ትግራይ ኣብ ሓደጋ ዘውድቕ ወራር ብምክያድ ጉጅለ ፋሽሽቲ ኣብዪ ኣሕመድ፣ ተስፋሕፋሕቲ ሓይልታት ትምክሕቲ ኣምሓርን መላፍንቱ ውልቀ መላኺ ኢሳያስን ኣብ ልዕሊ ህዝብን መንግስትን ትግራይ ዝፍፅምዎ ዘለዉ ግበን ዘርኢ ምፅናት፣ ግበን ኲናት፣ ግበን ኣንፃር ሰብኣውነትን ወራርን ንምምካትን ቃልስና ብዝበለፀ ንምጥንኻርን እቲ ኣብ ስራሕ ዘሎ ኣዋጅ ህፁፅ እዋን ምንዋሕን ዘለውዎ ክፍተታት ምምሕያሽን ኣድላዪ ምዃኑ ስለዝተኣመነሉ፣

ቤት ምኽሪ መንግስቲ ትግራይ ብመሰረት ዝተመሓየሸ ሕገ መንግስቲ ትግራይ ዓንቀፅ 39፣ 49/3/ሀ ን 103 ንኡስ ዓንቀፅ 3 ን ዝስዕብ መናውሕን መማሓየሽን ኣዋጅ ኣውፂኡ ኣሎ።

## ኣዋጅ ቁጥር 359/2014 ዓ.ም

## የትግራይ መንግስት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 358/2013 ዓ.ም ለማራዘምና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የትግራይ ህዝብ ህልውናና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ወረራ በማካሄድ የፋሽሽት አብዪ አህመድ ቡድን፣ የአማራ የትምክህት ተስፋፊ ሃይሎች እና ሸሪኩ አምባገነን ኢሳያስ በትግራይ ህዝብና መንግስት ላይ እየፈፀሙት ያለው የዘር ማጥፋት፣ የጦር ወንጀል፣ ፀረ-ሰብአዊነት ወንጀልና ወረራ ለመመከትና ትግላችን የበለጠ ለማጠናከር ስራ ላይ ያለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማራዘምና ያሉበትን ክፍተቶች ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን ስለታመነበት፣

የትግራይ መንግስት ምክር ቤት በተሻሻለው የትግራይ ህገ መንግስት አንቀፅ 39፣ 49/3/ሀ እና 103 ንኡስ አንቀፅ 3 መሰረት የሚከተለውን ማራዘሚያና ማሻሻያ አዋጅ አውጥቷል።

ዓንቀፅ 1· ሓጺር ርእሲ

እዚ ኣዋጅ "ቑፅሪ ኣዋጅ 358/2013 ዓ·ም ንምንዋሕን ንምምሕያሽን ዝወፅአ ቑፅሪ ኣዋጅ 359/2014 ዓ·ም" ተባሂሉ ክጥቀስ ይኽእል።

ዓንቀፅ 2· ትርጉም

1. "ኣዋጅ" ማለት ቑፅሪ ኣዋጅ ህፁፅ እዋን 358/2013 ዓ·ም እዩ።
2. "ስሪት" ማለት መንግስቲ ትግራይ ወራር ንምምካት ናብ በረኻ ምስ ወፅአ ንህዝባዊ መኽቲ ኣብ ሓደጋ ክውድቑ ዝኽእሉ ዓይነት ገበናትን ቕፅዓትን ዝደነገገ፣ ኣብ ቃልሲ ኮይንካ ክርአዩ ዝግበኦም ዋኒናት ፍትሃብሄር ዘቐመጠ፣ስልጣን ምድናይን ምስማዕ ይግበኣንን ከም ኣግባብነቱ ንማሕበራዊ ቤት ፍርዲ ወይ ንክርቢት ወይ ንኮሚቴ ፍትሕን ምክልኻል ገበንን ወይ ንኮሚቴ መኽተ ዝሃበ ኣካል እቲ ኣዋጅ ህፁፅ እዋን ዝኾነ ብመንግስቲ ትግራይ ዝወፀአን ኣብ መላእ ትግራይ ተፈፃምነት ዘለዎ ሕጊ እዩ።

ዓንቀፅ 3· መመሓየሺ

ኣዋጅ ህፁፅ እዋን ቑፅሪ 358/2013 ዓ·ም ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ።

1. ዓንቀፅ 2 ንኡስ ዓንቀፅ 9 እቲ ኣዋጅ ተሰሪዙ በዚ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 9 ተተኪኡ ኣሎ።

አንቀፅ 1. አጭር ርእስ

ይህ አዋጅ "አዋጅ ቁጥር 358/2013 ዓ.ምን ለማራዘምና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 359/2014 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀፅ 2. ትርጉም

1. "አዋጅ" ማለት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 358/2013 ዓ.ም ነው።
2. "ስሪት" ማለት የትግራይ መንግስት ወረራን ለመመከት ወደ በረሃ ከወጣ በኋላ ህዝባዊ መከተውን አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉትን አይነት ወንጀሎችና ቅጣት የደነገገ፣ በትግል ውስጥ ሆነህ ሊታዩ የሚገባቸው የፍትሃብሄር ጉዳዮችን ያስቀመጠ፣ የመዳኘት ስልጣንና ይግባኝን የመስማት እንደአግባብነቱ ለማህበራዊ ፍርድ ቤት ወይም ለክርቢት ወይም ለፍትህና የወንጀል መከላከል ኮሚቴ ወይም ለመከተ ኮሚቴ የሰጠ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ አካል የሆነ በትግራይ መንግስት የወጣና በመላው ትግራይ ተፈፃሚነት ያለው ህግ ነው።

አንቀፅ 3. ማሻሻያ

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 358/2013 ኢ.ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

1. የአዋጁ አንቀፅ 2 ንኡስ አንቀፅ 9 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ 9 ተተክቷል።

"9· 'ኣካላት ፍትሒ' ማለት ኮሚሽን ፖሊስ፣ ቢሮ ፍትሒ፣ ቤት ፍርዲ፣ ማሕበራዊ ቤት ፍርዲ፣ ኮሚሽን ምምሕዳር ኣብያተ ህንፀት፣ ማእኸል ኣብያተ ህንፀት ምስ መሓውሮም ዝሓውስ ኮይኑ ከም ኣድላይነቱ ኣብ ስራሕቲ ፍትሕን ምኽባር ልዕልነት ሕግን ንዝነጥፉ ኣብያተ ዕዮ መንግስቲ ክሓውስ ይኽእል።"

2. ዓንቀፅ 2 ንኡስ ዓንቀፅ 11 እቲ ኣዋጅ ተሰሪዙ በዚ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 11 ተተኪኡ ኣሎ።

"11· 'ገበን ኣንፃር ህልውና፣ ድሕንነትን ልኡላውነትን ህዝቢ ትግራይ' ማለት ኣብ ልዕሊ ህዝቢ ትግራይ፣ መንግስቲ ትግራይ፣ ብሕጋዊ መንገዲ ዝንቀሳቐስ ውድብ ፖለቲካ ትግራይ፣ መንግስታዊ ወይ ዘይመንግስታዊ ትካል ዝፍፀም ገበን ምዕናት ዘርኢ፣ ገበን ኲናት፣ ገበን ኣንፃር ሰብኣውነትን ወራርን፣ ገበን ራዕዲ፣ ገበን ሳይበር፣ ከቢድ ገበን ክትራን ወይ ሽፍትነት፣ ምስ ፀላኢ ምትሕብባር፣ ስለያ፣ ክድዓት ኢኮኖሚ፣ ምዝውዋር ወይ ምጥቃም ዘይሕጋዊ ዕጥቂ፣ ከቢድ ስርቂ፣ ኣብ ልዕሊ መሰረተ ልምዓት ጉድኣት ምብፃሕ፣ ባርዕ፣ ዝተወደቡ ገበናት፣ ምፍራስ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ትግራይ፣ ብዝኾነ ሰብ ዜግነቱ ወይ ዝመፅኣሉ ከባቢ ወይ

"9. 'የፍትህ አካላት' ማለት የፖሊስ ኮሚሽን፣ የፍትህ ቢሮ፣ ፍርድ ቤት፣ ማህበራዊ ፍርድ ቤት፣ የማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን፣ የማረሚያ ቤቶች ማእከል ከነ እርከኖቻቸውን የሚጨምር ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በፍትህና የህግ የበላይነት ማስከበር ስራዎች ላይ የተሰማሩ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ሊጨምር ይችላል።"

2. የአዋጁ አንቀፅ 2 ንኡስ አንቀፅ 11 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ 11 ተተክቷል።

"11. 'በትግራይ ህዝብ ህልውና፣ ደህንነትና ሉኡላዊነት ላይ የተቃጣ ወንጀል' ማለት በትግራይ ህዝብ፣ በትግራይ መንግስት፣ በህጋዊ መንገድ በሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ደርጅት፣ በመንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ላይ የሚፈፀም የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ የጦር ወንጀል፣ ፀረ-ሰብአዊነት ወንጀልና ወረራ፣ የሽብር ወንጀል፣ የሳይበር ወንጀል፣ ከባድ የዘረፋ ወንጀል ወይም ሽፍትነት፣ ከጠላት ጋር መተባበር፣ ስላለ፣ የኢኮኖሚ ክዳት፣ ህጋዊ ያልሆነ ትጥቅ ማዘዋወር ወይም መጠቀም፣ ከባድ ስርቆት፣ በመሰረተ ልማት ላይ ጉዳት ማድረስ፣ ቃጠሎ፣ የተደራጁ ወንጀሎች፣ የትግራይ ህገ መንግስታዊ ስርአት ማፍረስ፣ በማንኛውም ሰው ዜግነቱ ይሁን የመጣበት አካባቢ ግምት ውስጥ ሳይገባ መፈፀምን

ዝፈፀመሉ ቦታን ጊዜን ብዘየግድስ ዝፍፀም ዝሓውስ ኮይኑ ካልኦት መኸተ ንምጥንኻርን መሰል ህልውናን ድሕንነትን ህዝቢ ትግራይ ኣብ ሓደጋ ከውድቑ ዝኽእሉ ኣብ ሕጊ ገበን ዝተደነገጉ ይኹኑ ካብኡ ወፃኢ ተወሲኾቲ ገበናትን ቅፅዓቶምን ዝምልከት ደንቢ ብቤት ምኽሪ ፈፃሚ ስራሕ ይወፅእ።"

3. ዓንቀፅ 4 ንኡስ ዓንቀፅ 2 እቲ ኣዋጅ ተሰሪዙ ብዚ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ተተኪኡ ኣሎ።

"2· ድንጋገ እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 እንተሃለወ እውን እቲ ኣዋጅ ምስ መመሓየሺኡን ስዒቦም ዝወፅኡ ስሪትን ደንብን ወይ ካልኦት ኣብ ስራሕ ዘለዉ ሕግታት ብምጥሓስ ኣብ ህልውናን፣ ድሕንነትን ልኡላውነትን ህዝቢ ትግራይ ኣብ ዝኾነ ቦታን ጊዜን ገበን ኣብ ዝፈፀመ ዝኾነ ሰብ ተፈፃምነት ይህልዎ።"

4. ዓንቀፅ 5 ንኡስ ዓንቀፅ 2 እቲ ኣዋጅ ተሰሪዙ ብዚ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ተተኪኡ ኣሎ።

"2· ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝቐረበ ፃውዒት ክተተ ዝምልከት ዝርዝር ብቤት ምኽሪ ፈፃሚ ስራሕ እናተወሰነ ዝፍፀም ይኸውን።"

5. ኣብቲ ኣዋጅ ካብ ዓንቀፅ 6 ንኡስ ዓንቀፅ 2 ቐፂሉ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 3

ያካተተ ሆኖ ሌሎች መከተን ለማጠናከርና የትግራይ ህዝብ ህልውናና ደህንነትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል በወንጀል ህግ ያሉትንም ሆነ ከዚህ ውጭ ቅጣታቸውን የሚመለከት ደንብ በስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት ይወጣል።"

3. የአዋጁ አንቀፅ 4 ንኡስ አንቀፅ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ 2 ተተክቷል።

"2. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቢኖርም አዋጁን ከነማሻሻያው እና እነዚህ አዋጆች ተከትለው የሚወጡ ስሪትና ደንብ ወይም ሌሎች በስራ ላይ ያሉትን ህጎች በመጣስ በትግራይ ህዝብ ህልውና፣ ደህንነትና ሉኡላዊነት በማንኛውም ቦታና ጊዜ ሆኖ ወንጀል በፈፀመ ማንኛውም ሰው ላይ ተፈፃሚነት ይኖረል።"

4. የአዋጁ አንቀፅ 5 ንኡስ አንቀፅ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንኡስ አንቀፅ 2 ተተክቷል።

"2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 የቀረበ የክተት ጥሪ የሚመለከት ዝርዝር በስራ አስፈፃሚው ምክር ቤት እየተወሰነ የሚፈፀም ይሆናል።"

5. ከአዋጁ አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀፅ 2 ቀጥሎ የሚከተለውን አዲስ ንኡስ አንቀፅ 3

ተወሲኹ ኣሎ።

"3 · በቢ ግንባሩ፣ ንኡስ ግንባሩ፣ በቢ ከተምኡ፣ ክፍለ ከተምኡ፣ ወረድኡን ጣብያኡን ብማእኸላይ ኮማንድ ተጣይሸም ዝፀንሑ ኮሚቴታት መኸተ በቲ ኣዋጅ ክምዝተጣየሹ ዝቕፀር ኮይኑ በዝሖም፣ ተዋፅኦኦም፣ ስርሖምን ሓላፍነቶምን ብማእኸላይ ኮማንድ ዝውሰን ይኸውን።"

6. ዓንቀፅ 8 እቲ ኣዋጅ ተሰሪዙ በዚ ዝስዕብ ሓዱሽ ዓንቀፅ 8 ተተኪኡ ኣሎ።

"ዓንቀፅ 8. <u>ምቕራብ ፀብፃብ</u>

8· ቢሮ ፍትሕን ኣካላት ፀጥታን ብመሰረት እቲ ኣዋጅ ኣብ ትሕቲ ቁፅፅር ዝወዓሉ ሰባት ዀነታት ኣተሓሕዘኦም፣ ሽም ዝርዝሮምን ዘለውሉ ቦታን በቢ እዋኑ ንመርማሪ ቦርድ ፀብፃብ ናይ ምቕራብ ግቡእ ኣለዎም።"

7. ዓንቀፅ 9 ንኡስ ዓንቀፅ 3 እቲ ኣዋጅ ተሰሪዙ በዚ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 3 ተተኪኡ ኣሎ።

"3· ነዚ ኣዋጅ ስዒቦም ዝወፅኡ ደንቢ፣ መምርሕታትን ዝመሓላለፉ ውሳነታትን ኣብ ስራሕ ክውዕሉ ይገብሩ።"

8. ዓንቀፅ 11 ንኡስ ዓንቀፅ 3 ን 4ን እቲ ኣዋጅ ተሰሪዞም በዚ ዝስዕብ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 3ን 4ን ተተኪኦም ኣሎ።

ተጨምሯል።

"3. በየግምባሩ፣ ንኡስ ግንባሩ፣ በየከተማው፣ በየክፍለ ከተማው፣ በየወረዳውና ቀበሌው በማእከላይ ኮማንድ ተቋቁመው የቆዩ የመከተ ኮሚቴዎች በአዋጁ መሰረት እንደተቋቋሙ የሚቆጠር ሆኖ ብዛታቸው፣ ተዋፆአቸው፣ ስራቸውና ሃላፊነታቸውን በማእከላይ ኮማንድ የሚወሰን ይሆናል። "

6. የአዋጁ አንቀፅ 8 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 8 ተተክቷል።

"አንቀፅ 8. <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

8. የፍትህ ቢሮና ፀጥታ አካላት በዚህ አዋጅ መሰረት በቁጥጥር ስር የዋሉትን ሰዎች የአያያዝ ሁኔታቸው፣ ዝርዝር ስማቸውንና ያሉበት ቦታ በየጊዜው ለመርማሪ ቦርድ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።"

7. የአዋጁ አንቀፅ 9 ንኡስ አንቀፅ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ 3 ተተክቷል።

"3. አዋጁን ተከትለው የሚወጡ ደንብ፣ መመሪያዎች እና የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ።"

8. የአዋጁ አንቀፅ 11 ንኡስ አንቀፅ 3 እና 4 ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀፆች 3 እና 4 ተተክተዋል።

"3· ብገበን ኣንፃር ህልውና፣ ድሕንነትን ልኡላውነትን ህዝቢ ትግራይ ዝተጠርጠረ ወይ ዝተኸሰሰ ሰብ ብውሕስና ክወፅእ ኣይፍቀደሉን፤ ብዝኾነ ምኽንያት ኣብ ከይዲ ምዕራይ ወይ ክስን ኽርክርን ብውሕስና ክወፅእ ብታሕተዎት ኣብያተ ፍርዲ እንተተወሲኑን ብመርማሪ ወይ ዓቃቢ ሕጊ ይግባእኒ እንተሓቲቱን እቲ ውሳነ ተግባራዊ ከይኮነ ይፀንሕ፣

4.ገበን ኣንፃር ህልውና፣ ድሕንነትን ልኡላውነትን ህዝብን መንግስትን ትግራይ ዝምልከቱ ኣብዚ ኣዋጅን ስዒቡ ዝወፅእ ደንብን ወይ ዝበለፀ ቕፅዓት ዘቕፅዕ እንተደኣ ኾይኑ ኣብ ዝተፈላለዩ ኣብ ስራሕ ዘለዉ ሕግታት ዝተደንገጉ ዋኒናት ገበን ስልጣን ምድናይ ናይ ማሕበራዊ ቤት ፍርድን ስሩዕ ቤት ፍርድን ይኸውን፤ ሰበር መጋባእያ ላዕለዋይ ቤት ፍርዲ መንግስቲ ትግራይ ብሙሉእ ወይ ብኣብዝሓ ድምፂ ዝህቦ ውሳነ ናይ መወዳእታን ኣገዳድን ይኸውን።"

9.ዓንቀፅ 13 ንኡስ ዓንቀፅ 2፣ 3፣ 4፣ 6፣ 7ን 9ን እቲ ኣዋጅ ተሰሪዞም በዞም ዝስዕቡ ሓደሽቲ ንኡስ ዓንቀፃት 2፣ 3፣ 4፣ 6፣ 7ን 9ን ተተኪኦም ኣለዉ።

"2.ዝኾነ ሰብ ገበን ኣንፃር ህልውና፣ ድሕንነትን ልኡላውነትን ህዝቢ ትግራይ ብምፍፃሙ ጥፍኣተኛ ኮይኑ እንተተረኺቡ

"3. በትግራይ ህዝብ ህልውና፣ ደህንነትና ሉኡላዊነት በወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው በዋስ እንዲወጣ አይፈቀድለትም፤ በማንኛውም ምክንያት በምርመራ ወይም በክስና ክርክር ሂደት በዋስትና እንዲወጣ በስር ፍርድ ቤቶች ከተወሰነና ዓቃቤ ህግ ይግባኝ ከጠየቀ ውሳኔውን ተግባራዊ ሳይሆን ይቆያል፣

4. የትግራይ ህዝብና መንግስት ህልውና፣ ደህንነትና ሉኡላውነትን የሚመለከቱ ወንጀሎች በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ ወይም የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ከሆነ በተለያዩ በስራ ላይ ያሉ ህጎች የተደነገጉትን የወንጀል ጉዳዮች የመዳኘት ስልጣን የማህበራዊ ፍርድ ቤት እና የመደበኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፤ የትግራይ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ወይም በአብላጫ ድምፅ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና አስገዳጅ ይሆናል።"

9. የአዋጁ አንቀፅ 13 ንኡስ አንቀፅ 2፣ 3፣ 4፣ 6፣ 7 እና 9 ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንኡስ አንቀፆች 2፣ 3፣ 4፣ 6፣ 7 እና 9 ተተክተዋል።

"2.ማንኛውም ሰው በትግራይ ህዝብ ህልውና፣ ደህንነትና ሉኡላዊነት ወንጀል በመፈፀሙ

ክከም ዓይነት ገበኑን ከም ኣድላይነቱን ነዚ ኣዋጅ ስዒቡ ብዝወፅእ ደንብ ወይ ኣብ ስሩዕ ሕግታት ገበን ዝተደንገጉ ቅፅዓታት ይቕፃዕ፤ ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።

3. ዝበለፀ ቅፅዓት ዘቕፅዕ እንተኾይኑ ኣብ ሕጊ ገበን ወይ ኣብ ካልኦት ሕግታት ዝተደንገገ ተሓታትነት ገበን ሕሉው ኮይኑ ኣብዚ ኣዋጅን ስዒቡ ዝወፅእ ደንብን ዝተቐመጠ ግቡእ ምፍፃም ወይ ምትሕብባር ወይ ዝወሃቡ ውሳኔታት ወይ ስጕምትታት ዝተመሓላለፈ ሰብ ብገበን ተሓታቲ ይኸውን፤ ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን፣

4. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 3 ዝተደንገገ ገበን ዝተፈፀመ ብትካል እንተኾይኑ ነቲ ገበን ዝፈፀመ ወይ ኣብቲ ገበን ዝተሳተፈ ሰብ ዝተቐመጠሉ ቕፅዓት ማእሰርቲ ሕሉው ኮይኑ እቲ ትካል ብመቕፃዕቲ ገንዘብ ይቕፃዕ፤ መጠን ቅፅዓት ማእሰርትን ገንዘብን ብደንቢ ይውሰን፣

6. ኣብዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 3 ዝተደንገገ ገበን ዝተፈፀመ ብተሽከርካሪ እንተኾይኑ ነቲ ገበን ዝፈፀመ ወይ ኣብቲ ገበን ዝተሳተፈ ሰብ ብማእሰርቲ ዝተቐመጠሉ ቕፅዓት ሕሉው ኮይኑ ፍቓድ መዘወሪኡ ወይ ፍቓድ ንግዱ ክእገድ ወይ ክስረዝ

ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ እንደ ወንጀሉ አይነትና እንደአስፈላጊነቱ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ ወይም በመደበኛ የወንጀል ህጎች የተደነገጉትን ቅጣቶች ይቀጣል፤ ዝርዝሩ ብደንብ ይወሰናል።

3. የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ከሆነ በወንጀል ህግ ወይም በሌሎች ህጎች የተደነገገው የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ ላይ የተቀመጠ የመፈፀም ወይም የመተባበር ግዴታ ወይም የሚሰጡ ውሳኔዎችን ወይም እርምጃዎችን የተላለፈ ሰው በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

4. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 የተደነገገው ወንጀል የተፈፀመው በተቋም ከሆነ ወንጀሉን የፈፀመ ወይም በወንጀሉ የተሳተፈ ሰው የተቀመጠለትን የእስራት ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤ የእስራት ቅጣትና የገንዘብ መቀጮው መጠን በደንብ ይወሰናል፣

6. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 3 የተደነገገው ወንጀል የተፈፀመው በተሽከርካሪ ከሆነ ወንጀሉን የፈፀመ ወይም በወንጀሉ የተሳተፈ ሰው የተቀመጠለት የእስራት ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ የመንጃ ወይም የንግድ ፈቃዱን ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ

ይኽእል፤ ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን፣

7· ዓንቀፅ 13 ንኡስ ዓንቀፅ 1ን 2ን እቲ ኣዋጅ ብምትሕልላፍ ብዝፈፀሞ ገበን ጥፍኣተኛ ዝተበሃለ ሰራሕተኛ መንግስቲ ዝውሰኖ ቅፅዓት ማእሰርቲ ሕሉው ኮይኑ ብዘይካልእ ተወሳኺ ስነ ስርዓት ካብ ስርሑ ብቐጥታ ይባረር፣ እቲ ተግባር ምብራር ብፍሉይ ደንቢ ንዝመሓደሩ ሰራሕተኛታት እውን ዝሓውስ እዩ፤ እቲ ሰራሕተኛ ብቤት ፍርዲ ነፃ እንተተባሂሉ ብቤት ዕዮኡ ብዲስፐሊን ክሕተት ይኽእል፣

9· መምርሒ ኣወሳስና ቅፅዓትን ዝርዝር ስነ ስርዓትን ብላዕለዋይ ቤት ፍርዲ መንግስቲ ትግራይ ክወፅእ ይኽእል።"

10. ዓንቀፅ 14 ዝነበረ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ዝተገበረ ኮይኑ ሓዱሽ ንኡስ ዓንቀፅ 2 ተወሲኹ ኣሎ።

"ዓንቀፅ 14. <u>ዘይግደቡ መሰላት</u>

1. እዚ ኣዋጅን ስዒቡ ዝወፅእ ደንብን ተፈፃሚ ኣብ ዝኾኑሉ ጊዜ ኣብ ዓንቀፅ 103 ንኡስ ዓንቀፅ 4 ሕገ መንግስቲ ትግራይ ዝተደንገጉ መሰላት ኣይገሃሱን፣ ኣይጠሓሱን፣ ኣይግደቡን፣

2. ድንጋገ ንኡስ ዓንቀፅ 1 እዚ ዓንቀፅ ሕሉው ኮይኑ ካልኦት መሰላት ንኣፈፃፅማ እዚ ኣዋጅ ክበሃል ስዒቡ ብዝወፅእ ደንቢ ምግዳብ ይከኣል።"

ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣

7. የአዋጁ አንቀፅ 13 ንኡስ አንቀፅ 1 እና 2 በመተላለፍ በፈፀመው ወንጀል ጥፋተኛ የተባለ የመንግስት ሰራተኛ የሚወሰንበት የእስራት ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ያለ ሌላ ተጨማሪ ስነ ስርአት ከስራው በቀጥታ ይባረራል፣ የመባረር ተግባሩ በልዩ ደንብ የሚተዳደሩትን ሰራተኞችንም ይጨምራል፤ ሰራተኛው በፍርድ ቤት ነፃ የተባለ እንደሆነ በመስሪያ ቤቱ በዲስፐሊን ሊጠየቅ ይችላል፣

9. ዝርዝር ስነ ስርአትና የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በትግራይ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊወጣ ይቻላል።"

10. አንቀፅ 14 የነበረው ንኡስ አንቀፅ 1 የተደረገ ሲሆን አዲስ ንኡስ አንቀፅ 2 ተጨምሯል።

"አንቀፅ 14. <u>የማይገደቡ መብቶች</u>

1. ይህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብ ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ በትግራይ ህገ መንግስት አንቀፅ 103 ንኡስ አንቀፅ 4 የተደነገጉትን መብቶች አይገሰሱም፣ አይጣሱም፣ አይገደቡም፣

2. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች መብቶች ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል ቀጥሎ በሚወጣው ደንብ መገደብ ይቻላል።"

11. ካብቲ ኣዋጅ ዓንቀፅ 15 ቐጺሉ ሓዱሽ ዓንቀፅ 16 ዝተወሰኸ ኮይኑ ዓንቀፅ 16፣17ን 18ን ዝነበሩ ከም ቅደም ሰዓቦም ዓንቀፅ 17፣ 18ን 19ን ኮይኖም ተሸጋሺጎም ኣለዉ።

"ዓንቀፅ 16 <u>ስልጣን ዳይነት</u>

1. ስልጣን ዳይነት ዋኒናት ገበንን ፍትሃብሄርን ናይ ማሕበራዊ ቤት ፍርድን ሰሩዕ ቤት ፍርድን ይኸውን፣ ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን፣
2. ኣብ እዋን መኸተን ቓልስን ህዝቢ ትግራይ ብዝነበረ ስሪት ዝተወሰኑ ዋኒናትን ዝተወሰዱ ስጉምትታትን ብመሰረት እቲ ኣዋጅ ከምዝተፈፀሙ ይቑፀር፤ ዳግም ክርኣዩ፣ ክሲ ክቐርበሎምን ይግበኣኒ ክሕተተሎምን ኣይኽእልን፤ ዝርዝሩ ብደንቢ ይውሰን።'

12. ዓንቀፅ 17 ዝነበረ ዓንቀፅ 18 ኮይኑ ዝተሸጋሸገ እንትኾን ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ።

"ዓንቀፅ 18. <u>ስልጣን ምውፃእ ደንብን መምርሕን</u>

1. ቤት ምኽሪ ፈፃሚ ስራሕ ብመሰረት እቲ ኣዋጅ ምስ መመሓየሺኡ ብዝተወሃቦ ስልጣን ደንቢ የውፅእ፣
2. ቤት ምኽሪ ፈፃሚ ስራሕ ኣድላዪ ኮይኑ እንተረኺብዎ ነቲ ኣዋጅ ምስ መመሓየሺኡ መፈፀሚ ዝኸውን ዝርዝር መምርሒ ከውፅእ·

11. ከአዋጁ አንቀፅ 15 ቀጥሎ አዲስ አንቀፅ 16 የተጨመረ ሲሆን አንቀፅ 16፣ 17 እና 18 የነበሩትን እንደ ቅደም ተከላቸው አንቀፅ 17፣18 እና 19 ሆነው ተሸጋሽጓል።

"አንቀፅ 16. <u>የዳኝነት ስልጣን</u>

1. የወንጀል እና የፍትሃብሄር ጉዳዮች የዳኝነት ስልጣን የማህበራዊ ፍርድ ቤትና የመደበኛ ፍርድ ቤት ይሆናል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣
2. በትግራይ ህዝብ የመከትና የትግል ጊዜ በነበረው ስሪት መሰረት የተወሰኑ ጉዳዮችና የተወሰዱ እርምጃዎች በአዋጁ መሰረት እንደተፈፀሙ ይቆጠራል፤ እንደገና ሊታዩ፣ ክስ ሊቀርብባቸውና ይግባኝ ሊጠየቅባቸው አይችልም፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።"

12. አንቀፅ 17 የነበረው አንቀፅ 18 ሆኖ የተሸጋሸገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

"አንቀፅ 18. <u>ስልጣን ምውፃእ ደንብን መምርሕን</u>

1. የስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት በአዋጁ ከነ ማሻሻያው በተሰጠው ስልጣን መሰረት ደንብ ያወጣል፣
2. የስራ አስፈፃሚ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአዋጁን ከነማሻሻያው ማስፈፀሚያ የሚሆን ዝርዝር መመሪያ

ይኽእል።"

13. ዓንቀፅ 18 ዝነበረ ዓንቀፅ 19 ኮይኑ ዝተሸጋሸገ እንትኾን ከምዝስዕብ ተመሓይሹ ኣሎ።

"ዓንቀፅ 19. ተፈፃምነት እቲ ኣዋጅ

1. ተፈፃምነት እቲ ኣዋጅ በቲ ዘጋጠመ ኣገዳዲ ኩነታት ከኣ ካብ ሕዳር 1/2013 ዓ.ም ጀሚሩ ክሳብ ሓምለ 16/2013 ዓ.ም ይኸውን፣

2. ድንጋገ እዚ ዓንቀፅ ንኡስ ዓንቀፅ 1 ሕሉው ኮይኑ እቲ ኣዋጅ ካብ ሓምለ 17/2013 ዓ.ም ጀሚሩ ንዝቕፅሉ ሽዱሽተ ኣዋርሕ ኣብ ስራሕ ክፀንሕ ይኽእል፣

3. እቲ ኣዋጅ ምስ መማሓየሺኡ ካብ ጥሪ 17/2014 ዓ.ም ጀሚሩ ንዝቕፅል ኣርባዕተ ኣዋርሕ ኣብ ስራሕ ክፀንሕ ይኽእል፤ ይኹን እምበር ኣድላዪ ኮይኑ እንትርከብ ቤት ምኽሪ ፈፃሚ ስራሕ ኣብ ዝኾነ ጊዜ ብሙሉእ ወይ ብኽፋል ክቋርፆ ይኽእል።"

ደብረፅዮን ገብረሚካኤል (ዶ/ር

ፕሬዚደንት መንግስቲ ትግራይ

ሊያወጣ ይችላል።"

13. አንቀፅ 18 የነበረው አንቀፅ 19 ሆኖ የተሸጋሸገ ሲሆን እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

"አንቀፅ 19. የዚህ አዋጁ ተፈፃሚነት

1. የአዋጁ ተፈፃሚነት ባጋጠመው አስገዳጅ የጦርነት ሁኔታ ምክንያት ከህዳር1/2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሃምሌ 16/2013 ዓ.ም ይሆናል፣

2. የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጁን ከሃምሌ 17/2013 ዓ.ም ጀምሮ ለሚቀጥሉት ስድስት ወራት በስራ ላይ ሊቆይ ይችላል፣

3. አዋጁ ከነ ማሻሻያው ከጥር 17/2014 ዓ.ም ጀምሮ ለሚቀጥሉት አራት ወራት በስራ ላይ ሊቆይ ይችላል፤ ይሁን እንጂ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የስራ አስፈፃሚው ምክር ቤት በማንኛውም ጊዜ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያቋርጠው ይችላል።"

ደብረፅዮን ገብረሚካኤል (ዶ/ር)

የትግራይ መንግስት ፕሬዚደንት